# የቅመማ-ቅመማት ጉዳይ

ሰውን ፍለጋ
ላይ ታቹን ዞሬ
ብዙ ደክሜ
ጥሬና ግሬ
የቀረበኝስ
ቁንዶ-በርበሬ

ቅመሙን ሁሉ
ምን ብወደው
የምመኘውን
የት አገኘው
የመረጥኩትስ
በሶ-ብላው

ላዩን በሰቃ
ታቹን ቃሊቲ
ከወልቂጤና
ከወሎ ባቲ
የተስማማኝስ
ጦስኝ፣ አሪቲ

ረክሶ ቢረክስ
ወይ ቢወደድ
ቢያንስም ቢበዛ
ዘመድ አዝማድ
የምፈልገው
ጥቁር አዝሙድ

የምን መማጠን
ይሂድ ቢሻው
ያገኛት የለ
እንደ ሥራው

ድምብላሉና
ኮረሪማው

አጉል መድከሙ
ወድቆ ለጠፋ
ይቅርብኝ በቃ
ከንቱ አልልፋ
ይልቅ አምጡልኝ
ቅርንፉድ፣ ቃርፋ

እትነካኩት
ያ ቅመሙን
ሊቀ ጳጳሱ
የኛ አቡን
ጉዳዬን ለኔ
ንጥር ካሙን

የምወደው
አገኘሁ ፊውሴ
የማኝከው
ነክሼ ጥርሴ
የሚጥመው
ያ ደማከሴ

በየዓይነቱ
ሰባት-ቅመም
ተቀላቅሏል
በዚህች ዓለም
አገኘሁታ
ጤና አዳም

ገ/ኢ. ጐርፉ።